ሰብዓዊ መብቶችን እና ዲሞክራሲን በመደገፍ በ2006 የዩናይትድ ስቴትስ ክንዋኔ ዘገባ

1. መግቢያ
2. የአሜሪካ የሰብዓዊ መብቶች እና የዴሞክራሲ ስትራቴጂ
3. አፍሪካ
4. ኢትዮጵያ

ሰብዓዊ መብቶችን እና ዲሞክራሲን በመደገፍ በ2006
የዩናይትድ ስቴትስ ክንዋኔ ዘገባ

መግቢያ

ሰብዓዊ መብቶችን እና ዴሞክራሲን በመደገፍ በ2006 ዓ.ም. የዩናይትድ ስቴትስ ክንዋኔ፡ በዴሞክራሲ፣ሰብዓዊ መብቶች እና የሠራተኛ ቢሮ ይፋ የተደረገ፡፡

". . . መሻሻል ብዙውን ጊዜ ካለ ታላቅ ፈተና የማይገኝ በመሆኑ፣ ለውጥ ለማምጣት ግፊት የሚያደርጉ ወገኖችን ግትርነት እና ብሎም ጠንካራ አፈና ይጋረጠባቸዋል፡፡ መያዶች እና ሌሎችም የሰብዓዊ መብቶች ተከላካዮች ከበባ ውስጥ በሚወድቁባቸው ጊዜያት ነፃነት እና ዴሞክራሲ ይሸረሸራሉ፡፡ የዓለም ዴሞክራሲዎች ይኽን መቀልበስ አለባቸው፡፡ እኛ ለተከላካዮች መከላከል አለብን፡፡"

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮንዶሊዛ ራይስ
ታህሣሥ 5 ቀን 1999 ዓ.ም.
ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶችን ቀን በማሰብ

ይህ ዘገባ በ2006 ዓ.ም. ውስጥ በመላው ዓለም የሰብዓዊ መብቶችን መከበር ለማበረታታት እና ዴሞክራሲን ወደፊት ለማራመድ ዩናይትድ ስቴትስ በብዙ መንገድ የፈጸመችውን ይመዘግባል፡፡

ፕሬዚደንት ቡሽ በነፃነት ላይ የተመሠረተ የውጭ ፖሊሲ እንድንመራ ሲያደርጉ፣ሰብዓዊ መብቶችን እና ዴሞክራሲን ማራመድ የብሔራዊ ደኅንነታችን ስትራቴጂ ዋነኛ ነገር መሆኑን ለይተው አስቀምጠውታል፡፡ ፕሬዚደንቱ እንደተናገሩት "ከሁሉም በበለጠ እያንዳንዱ ሽብርተኛ የሚፈራው ሰብዓዊ ነፃነትን --- ወንዶች እና ሴቶች የእራሳቸውን ምርጫዎች የሚያደርጉበት፣ በሕሊናቸው የሚመሩበት፣ በጥላቻዎቻቸው ሳይሆን፣ በተስፋዎቻቸው የሚኖሩባቸው ማኅበረሰቦች መኖራቸውን ነው፡፡"

በ2006 ዓ.ም. በሙሉ፣ በዓለም ውስጥ በሚገኙት አህጉራት ሁሉ፣ ዓለምአቀፋዊ የሰብዓዊ መብቶች ደረጃዎችን እና ዴሞክራሲያዊ መርሆዎችን ወደፊት ለማራመድ እና እነዚህንም ከመቀልበስ ለመከላከል ሞክረናል፡፡ የሚመሳሰሉን

ዴሞክራሲዎች ተጠያቂነት ያለባቸው መንግሥታዊ ተቋሞችን እና የሕግ የበላይነትን (ሩል ኦፍ ሎው) እንዲመሰርቱ ረድተናል። የነፃ እና ትክክለኛ ምርጫ ሂደት እንዲኖር እና፣ ሴቶችንና አናሳዎችን ጨምሮ፣ ዜጎች በሙሉ በአገሮቻቸው ሕይወት ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርጉ አበረታትተናል። ሲቪል ማኅበረሰቦችን ለማጠናከር እና የመገናኛ አውታሮችን ነፃነት ለማራመድ ሠርተናል። ከእነዚህም በተጨማሪ፣ ሰብዓዊ መብቶች እና የዴሞክራሲ መርሆዎች ከበባ በተደረገባቸው ሥፍራዎች ሰላማዊ ለውጥ እንዲመጣ ግፊት የሚያደርጉ ወገኖችን በመደገፍ አብረን ቆመናል።

ለሰብዓዊ ክብር መከላከል እና በዓለም ውስጥ ጠንካራ ዴሞክራሲዎች እንዲያድጉ ማድረግ የረጅም ግዜ ጥረትን ይጠይቃል። እንደዚሁም ከሌሎች መንግስታት፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ከግሉ ዘርፍ ጋር በአጋርነት መስራትን ይጠይቃል። መሰናክሎች ይኖራሉ፣ መሻሻልም አንዳንድ ጊዜ አዝጋሚ ቢሆንም፣ እኛ እና አጋሮቻችን በጽናት እንቆማለን። ይህንንም የምናደርገው የነፃነትን ትሩፋት ለእራሳቸው፣ ለልጆቻቸው እና ለአገሮቻቸው ለዘለቄታው ለማረጋገጥ በሚጓጉት ከሁሉም ባህልና ቀለም፣ ከሁሉም የኋላ ታሪክ እና እምነት፣ በሆኑት ወንዶችና ሴቶች ህልም ላይ መመስረት ትክክለኛ እና ብልህነት መሆኑን ስለምናምንበት ነው።

በእነዚህ ሃሳቦች ላይ በመመሥረት፣ በ2006 ዓ.ም. ስቴት ዲፓርትመንት (የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሰብዓዊ መብቶችን እና ዲሞክራሲን የደገፈ ስለመሆኑ የተጠናቀረውን ዘገባ በዚህ አማካይነት ለዩናይትድ ስቴትስ ኮንግሬስ አስተላልፋለሁ።

ኮንዶሊዛ ራይስ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር
መጋቢት 27 ቀን 1999 ዓ.ም. ይፋ የተደረገ

የአሜሪካ የሰብዓዊ መብቶች እና የዴሞክራሲ ስትራቴጂ

ሰብዓዊ መብቶችን እና ዴሞክራሲን በመደገፍ በ2006 ዓ.ም. የአሜሪካ ክንዋኔ፡ በዴሞክራሲ፣ ሰብዓዊ መብቶች እና የሠራተኛ ቢሮ ይፋ የተደረገ።

ሰብዓዊ መብቶችን እና ዴሞክራሲን መደገፍ፡- በ2006 ዓ.ም. የአሜሪካ ክንዋኔ መላውን ዓለም በማቋረጥ በአገር ውስጥ የመሻሻል ጥረቶችን ለመደገፍ ባለፈው ዓመት የተጠቀምንባቸውን በርካታ የዲፕሎማቲክ መሣሪያዎች ይገልጻል።

ግለሰብዓዊ እና ዴሚክራሲያዊ ነፃነቶችን ወደፊት ለማራመድ አንድ ወጥ የሆነ ቀመር (ፎርሙላ) የለም። ጥረቶቻችን ሰብዓዊ መብቶችን በሚገባ ለመጠቀም እና ለመጠበቅ እንዲቻል በግብር ላይ ባለ ዴሞክራሲ ውስጥ እንዲኖሩ በሚያስፈልጉ እና ተያያዥ በሆኑ ሦስት ዋነኛ ነገሮች ላይ አትኩረዋል። አንደኛ፣ እውነተኛ /ሃቀኛ ውድድር መደረጉን ለማረጋገጥ በተደላደለ የመንቀሳቀሻ መስክ ላይ የነፃ እና ትክክለኛ ምርጫዎች መደረግ። ሁለተኛ፣ ነፃ የሕግ አውጭ እና የፍትሕ ሥርዓትን ጨምሮ፣ በሕግ የበላይነት ሥር ተወካይነትን፣ ግልፅነትን እና ሃላፊነትን ያካተተ መልካም አስተዳደር። ሦስተኛ፣ መንግስት እውነተኛ ሆኖ እንዲሠራ፣ ዜጎች ተሳታፊዎች እንዲሆኑ፣ መሻሻሎች መስመራቸውን እንዳይስቱ የሚያደርግ ጠንካራ ሲቪል ማሕበረሰብ መኖር። እነዚህ ሦስቱ ዋነኛ የሆኑ የዴሞክራሲ ቀመሮች ደካማ ሆነው በሚገኙባቸው ሥፍራዎች እነሱን ለማጠናከር ሠርተናል። በከበባ ስር በወደቁባቸው ሥፍራዎች ልንከላከልላቸው ጥረናል። በመንግስት አፈና የተነሳ ከላይ የጠቀስናቸው ከነጭራሹ በሌሉባቸው ሥፍራዎች ደግሞ ከነፃነት ህልማቸው ጋር በፍርሃትና ሰቀቀን ስለሚኖሩት ድምፃችንን ከፍ አድርገን አሰምተናል።

እነዚህ ሁሉ የሚያሳዩት ለሰብዓዊ መብቶች እና ለዴሞክራሲ የሰጠነው ድጋፍ በእያንዳንዱ አገር እና አህጉር ለተጋረጡት ፈተናዎች በተለይ የተዘጋጀ እንደነበረ ነው። ለምሳሌ፣ በምዕራቡ የአለም አጋማሽ ዋናው ፈተና የዴሞክራሲያዊ መሻሻል ስለሆነ፣ ዜጎቻቸው ለተሻለ ሕይወት የሚያቀርቧቸውን ጥያቄዎች ማሟላት እንዲችሉ አቅማቸውን እንዲገነቡ ረድተናል። ለሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ መሻሻል እና የመንግስታዊ ማሻሻልንም ወደፊት ለማራመድ ሁከት እና ብጥብጥን ማቆም ለብዙዎቹ የአፍሪካ አገሮች ወሳኝ ነው። በደቡብ፣ ማዕከላዊ እና ምስራቅ እስያ እና በፓሲፊክ አቋራጭ ሰብዓዊ መብቶችን እና ዴሞክራሲን

የሚፈታተኑዋቸው በዚያ በጣም ሰፊ አካባቢ የሚገኙትን አገሮች ብዛት ያህል የተለያዩ ናቸው። ብዙዎቹን በሚመለከት፣ የመልካም አስተዳደር ጉዳዮችን በተሻለ ሁኔታ እንዲወጡ እና እስከ አሁን ያከናወኑትንም ማሻሻል በይበልጥ እንዲያጠናክሩ ዴሞክራሲዎችን አግዘናል። በሌላ በኩል ደግሞ መሪዎች በዜጎቻቸው መብቶች ኪሣራ የአገዛዝ እዛቡን በያዙባቸው ሥፍራዎች የሚፈጸሙትን ግፎች እየለየን በማሳየት፣ ሕዝቦቹም በዓለም ውስጥ ከሚዘዋወሩት ሃሳቦች እና መረጃዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ሠርተናል። በአውሮፓ ከጅምሩ ምሉዕ፣ ነፃ እና ሰላም የሰፈነበት አህጉር እንዲኖራቸው ያላቸው ራዕይ እንዲሟላ ከአውሮፓውያን አጋሮቻችን ጋር መተባበራችንን ቀጥለናል። በሰፊው መሃል ምስራቅ እና በሰሜን አፍሪካ አህጉር ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የትምህርት መሻሻል እንዲኖር፣ ሰፋ ባለው መካከለኛው ምሥራቅ እና የሰሜን አፍሪካ አህጉር ሽንጎ ለወደፊት እና የመካከለኛው ምስራቅ አጋርነት በራስ ተነሳሽነትን በመሳሰሉ አዳዲስ በሆኑ የባለ ብዙ እና የሁለት ወገን ጥረቶች አማካይነት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ እና የትምህርት ማሻሻል እንዲደረግ በመፈለግ እየጎለበተ ለመጣው የሕዝብ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ሰጥተናል።

እንደዚሁም በ2006 ዓ.ም. ውስጥ ሰብዓዊ መብቶችን እና የዴሞክራሲ ተከላካዮችን በመደገፍ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ራይስ ከፍተኛ የሆኑ በእራስ ተነሳሽነትን አስታውቀዋል። እነዚህም የሕዝባዊ መብቶች ተከላካዮች የገንዘብ ድርጅት (ፈንድ) ፣ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማስተናገድ አንፃር መንግስታት የሚመሩባቸው 10 የመያድ መርሆዎች ናቸው።

የሰብዓዊ መብቶች ተካላካዮች ፈንድ አንድ መንግስት በሚያደርገው አፈና የተነሳ የሰብዓዊ መብቶች ተከላካዮች ለሚያሻቸው ከፍተኛ ፍላጎቶች እንዲያውሉት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር (ስቴት ዲፓርትመንት) በፍጥነት አነስተኛ ገንዘብ እንዲሰጣቸው ያስችለዋል። ለዚህ ተግባር የሚውለው ከመነሻው 1.5 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲሆን፣ ገንዘቡ እንደ አስፈላጊነቱ በየዓመቱ የሚሟላ ሆኖ፣ ለሕጋዊ መከላከያ ወይም ለሕክምና ወጭዎች፣ ወይም ደግሞ የትግሉ አንቀሳቃሽ የሆኑትን ቤተሰቦች ጊዜ የማይሰጡ ፍላጎቶች ለአጭር ጊዜ ለመደገፍ የሚውል ይሆናል።

አሥሩ የመያድ መመሪያ መርሆች እኛ እራሳችን መያዶችን በማስተናገድ ረገድ የምንመራባቸው ሆነው፣ እንደዚሁም ሌሎች መንግስታት በዚህ አንፃር የሚወስዷቸውን እርምጃዎች የምንመዝንባቸው ይሆናሉ። መርሆዎቹም መያዶችን እና ሌሎች የሰብዓዊ መብቶች ተከላካዮችን በሚመለከት ረጅም እና በጣም ዝርዝር የሆኑትን የተመድን (የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን) እና ሌሎች ዓለምአቀፋዊ ሰነዶችን እንዲያሟሉ የተሰናዱ ናቸው። 10 የመያድ መርሆዎችን በማዘጋጀት እኛ ያበረከትነው አስተዋፅኦ ለመንግስታት፣ ዓለምአቀፋዊ ድርጅቶች፣ ለሲቪል ማኅበረሰብ ስብስቦች እና ለጋዜጠኞች የቅርብ መረጃ በመሆን፣ እየታገሉ ለሚገኙት መያዶች በዓለም ዙሪያ ድጋፍ ለማሰባሰብ ይረዳል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ሰብዓዊ መብቶችን እና ዴሞክራሲን ወደፊት ለማራመድ ከሁሉም በበለጠ እጅግ የሚያስፈልገው በአገሮቻቸው ውስጥ ለውጥ ለማምጣት የወንዶች እና የሴቶች ቆራጥነት እና ፅኑነት ነው። እንደዚሁም መሻሻል በዓለም ውስጥ በሚገኝ እያንዳንዱ አህጉር የአሜሪካን እና መሰል ዴሞክራሲዎችን የማያቋርጡ የጋራ ጥረቶችን ይጠይቃል። ከፊታችን ያለው መንገድ በአብዛኛው ቀጥተኛ አይሆንም። ያልተጠናከሩ ዴሞክራሲዎች ይቃብዛሉ/ይፍረከረካሉ። መሪዎቻቸው ለዴሞክራሲ ምሉዕ የሆነ ፅኑነት የሌላቸው አገሮች ወደ ኋላ ሊንሸራተቱ ይችላሉ። መሻሻልን ለማምጣት ግፊት የሚያደርጉት ወገኖች ለውጥ እንዲመጣ በማይፈልጉት ወገኖች ወደ ኋላ መገፋት አይቀሬ ይሆናል። እነዚህ የሚያሳስቡ እውነታዎች ናቸው። ያም ሆኖ፣ ለነፃነት አላማ እና ግብ የምናከናውነው ተግባር በዓለም አቋራጭ ለሚገኙ ወንዶች እና ሴቶች አዲስ እና ተስፋ የሚሰጡ እውነታዎችን ለመፍጠር ይረዳል ብለን እናምናለን።

መጋቢት 27 ቀን ይፋ የሆነ

አፍሪካ

ሰብዓዊ መብቶችን እና ዴሞክራሲን በመደገፍ በ2006 ዓ.ም. የአሜሪካ ክንዋኔ

በዴሞክራሲ፣ ሰብዓዊ መብቶች እና የሠራተኛ ቢሮ ይፋ የተደረገ።

"ኢ-ፍትሐዊነትን፣ ሙስናኛነትን እና የተዛባ አስተዳደርን.... በመቃወም መናገሬን ማስቆም የሚችሉ ከመሰላቸው ተሳስተዋል። ምንም አያስቆመኝም።"

ትሬቨር ንኪቤ፣ በመንግስት የተዋከበ የዝምባብዌ ጋዜጠኛ

ብዙ የአፍሪካ አገሮች ለአህጉሩ አዲስ ተስፋ በሚያመጣ ሁኔታ በዴሞክራሲ ጎዳና ተጨባጭ እመርታ አድርገዋል። ከ40 ዓመታት በላይ ከሆነ ጊዜ በኋላ የኮንጎ ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ተአማኒነት ያላቸው ፕሬዝደንታዊ እና የሕግ አውጭ ምክር ቤት ምርጫዎችን አካሂዳለች። በቤኒን፣ በማዳጋስካር እና በሞርታኒያ የተደረጉት ዴሞክራሲያዊ ምርጫዎች በአህጉሩ ቀናን ነገር የመጠበቅን አዝማሚያ እንደገና አድሶታል። አገሮች ወደ በለጠ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር እያመሩ ባሉበት ወቅት፣ የአሜሪካ እርዳታ ፖለቲካዊ ብዙሃንነትን በመገንባት፣ የድምፅ ሰጭዎች ምዝገባን ፣ እና የምርጫ ተከታታዮችን በመስጠት ላይ አትኩሯል። በዐጋንዳ ባለብዙ ፓርቲ የፖለቲካ ስርዐት ለመመስረት ዐጋንዳውያን ያደረጉትን ውሳኔ ለመደገፍ፣ አሜሪካ የድምፅ ሰጭዎችን ተሳትፎ እና የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶች በመቻቻል አብሮ መኖርን ለማጠናከር፣ እና የፕሬዝደንታዊ እና ፓርሊያሜንታዊ ምርጫዎችን አመራር ለማሻሻል የገንዘብ መስጠት ፕሮግራም ዘርግታለች። ያም ሆኖ በአህጉሯ ዴሞክራሲያዊ ማሻሻልን ተቋማዊ ማድረግ እጅጉን ፈታኝ እንደሆነ ቆይቷል።

ቁልፍ የሆኑ የሰብዓዊ መብቶች ችግሮች፣ በተለይም የጦር ግጭት በመላው አፍሪካ ቀጥሏል። በቻድ፣ ኮትዲቯር፣ በማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ፣ የኮንጎ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ፣ ሶማሊያ፣ እና ዑጋንዳ አሜሪካ ቅድሚያ የሰጠቻቸው ጉዳዮች ለብዙዎቹ ሕይወት እና አኗኗር አስጊ የሆነው ነውጥ እና ብጥብጥ እንዲያቆም ማድረግ፣ ለጥቃት የተጋለጡትን ሕዝቦች ከተጨማሪ ሰቆቃ መከላከል፣ እና ወደ አህጉሩ ሰላምና መረጋጋት ማምጣትን ያካትታሉ። በሰኔ ወር መግቢያ ጋምቢያ ለታዳጊ አገሮች የተነጣጠረ እርዳታ ከሚሰጠው የአሜሪካ

መንግስት ንብረት ከሆነው ኮርፖሬሽን፣ ከሚሊኒየም ፈተና ኮርፖሬሽን ተጠቃሚነት ታገደች። ይኽም የተደረገው በፀደይ ወራት ተሞክሮ ከከሸፈው መፈንቅለ መንግስት በኋላ የሲቪል እና የፕሬስ ነፃነቶችን ካጠበበች በኋላ ነው።

የዳርፉር የሰላም ስምምነት በሚያዝያ 27 ቀን የተፈረመ ቢሆንም፣ በዳርፉር ዘር ማጥፋት እንደቀጠለ ነው። በ2006 ዓ.ም. ውስጥ በሰላም ድርድር፣ የተመድ የፀጥታ ምክር ቤት በሚወስደው እርምጃ፣ እና በዳርፉር ውስጥ ፈርጠም ያለ ዓለምአቀፋዊ የሰላም ጥበቃ ኃይል እንዲሰማራ ጠንካራ ግፊት እና ድጋፍ በመስጠት፣ ሁከትን ለማስቆም እና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ንፁሀን ሰላማዊ ሰዎችን ሕይወት ለመከላከል፣ አሜሪካ በዲፕሎማስያዊ እና በሰብዓዊ ጥረቶች አለምአቀፋዊ ማህበረሰብን መርታለች። በዓለም ከሚገኙት አገሮች ሁሉ ለሱዳን ሰብዓዊ ዕርዳታ በመስጠት አሜሪካ ከፍተኛውን ልገሳ በማበርከት ቀጥላለች። በዝምባብዌ፣ ገዥው ፓርቲ የአስፈፃሚውን ቅርንጫፍ ሥልጣን በብቸኝነት ይዞ በሚገኝበት ሁኔታ፤ፓርሊያመንት፣ የፍትሕ ሥርዓቱ እና የአካባቢ መስተዳድሮች በአንዳንድ አሰራር ነፃ ሆነው ለመንቀሳቀስ የማያደርጉትን ጥረት አሜሪካ አበረታታለች። የፓርሊያመንት ኮሚቴዎችን ለማጠናከር በአሜሪካ የተቀየሰው እና የተደገፈው ፕሮግራም ተቃዋሚው ወገን እና መሻሻል እንዲኖር የሚፈልጉ የገዥው ፓርቲ አባላት ክርክራቸውን ከፍ እንዲያደርጉ በመርዳት፣ ከፓርሊያሜንት በሚቀርብ ሕግ ላይ ሕዝብ አስተያየት እንዲሰጥበት በማድረግ፣ ይበልጥ ግልፅነት እንዲኖር አበረታትቷል። እንደዚሁም የአሜሪካ ፕሮግራም በሴራ ሊዮን በቅርቡ እንደገና በተዋቀረው የሕዝብ መሰረተ ልማት በጣም አስፈላጊ የሆኑ ስልጠናዎችን ለአካባቢ መስተዳድር መሪዎች በመስጠት ማዕከላዊው መንግስት መሻሻሉን በቀጠለበት ጊዜ የከተማ እና የወረዳ ምክር ቤቶች ጤናን እና የግብርና አገልግሎቶችን ጨምሮ፣ በአካባቢ አስተዳደር ጉዳዮች ይበልጥ ሃላፊነቶች እንዲኖራቸው ረድቷል።

ዘላቂ ለሆነ ዴሞክራሲያዊ መረጋጋት ዋነኛ ዋስትናው ንቁ እና ተሳታፊ የሆነ ሲቪል ኅብረተሰብ ነው። አሜሪካ በመላው አፍሪካ ማህበረሰቦች ውስጥ የሲቪክ ትምህርት እንዲጠናከር የአገር ውስጥ መያዶችን፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እና የሰራተኛ እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ፣ ሲቪክ ማህበረሰቦች እንዲያድጉ፣ ለማህበረሰቦች የተለያዩ የመረጃ ምንጮች እንዲኖሩ ለማድረግ ሠርታለች። ለምሳሌ፣ በአሜሪካ በተሰጠ ገንዘብ የተደገፉ የአገር ውስጥ መያዶች

በሰብዓዊ መብቶች፣ በኤች አይቪ/ ኤይድስ፣ በእርቅ እና በሰላም ግንባታ ላይ በላይቤሪያ በሙሉ ለማህበረሰቦች ትምህርት ሰጥተዋል።

የአሜሪካ ፕሮግራሞች በአህጉሩ ነፃ፣ በኢኮኖሚው የተረጋጋ፣ ጎብረተሰብዓዊ ሃላፊነትን የተላበሰ የዜና ማሰራጫ (ሚዲያ) እንዲያድግ ረድተዋል። አሜሪካን በመጎብኘት የባለሙያዎች ልውውጥ ፕሮግራም አፍሪካውያን ጋዜጠኞች ተሳትፈዋል። 500 ያህል ጋዜጠኞች ዘገባቸውን እንዲያሻሽሉ አሜሪካ በኮንጎ ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ አሥራ ሁለት የአሠራር ማሳያዎችን (ወርክሾፕስ) ከማካሄዷም በተጨማሪ፣ አንድ የኢንተርኔት ስልጠና ትምህርት ሰጥታለች። እንዲሁም በአሜሪካ የተደገፉ ፕሮግራሞች በዝምባብዌ፣ በቻድ፣ በሞሪታኒያ፣ በጋምቢያ፣ በሴራ ሊዮን ፣ እና በኢትዮጵያ ነፃ እና ወገናዊ ያልሆነን መረጃ ፍሰት ለማራመድ እገዛ አድርገዋል።

በአህጉሩ ውስጥ በሚገኙት ብዙ አገሮች አስቸጋሪ ለሆነው ጉቦኛነት/ሙሰናኛነት ምላሽ በመስጠት፣ አሜሪካ በአፍሪካ ውስጥ የሚገኙ የሕግ ሥርዓቶች ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና እና ግልፅ እንዲሆኑ ለማድረግ የዕርዳታዋ ተቀዳሚ አድርጋለች። በቻድ በነዳጅ ገቢ ለሚሰሩ ዕቅዶች ተጠያቂነትን ለማራመድ አሜሪካ ለነዳጅ ገቢ አመራር ኮሌጅ የቴክኒክ እርዳታ ከመስጠቷም በተጨማሪ፣ ለፓርሊያመንት አባላት የበጀት ዝግጅት ሥልጠና ያስፈለገውን ገንዘብ ሰጥታለች። እንደዚሁም አሜሪካ በዛምቢያ፣ በቻድ፣ በላይቤሪያ፣ እና በጋምቢያ የሚደረጉትን የፀረ-ሙስና ጥረቶች በገንዘብ ደግፋለች።

የሴቶችን፣ የእናቶችን፣ እና የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ጨምሮ፣ አሜሪካ ለሰብዓዊ መብቶች መጠበቅ የምትሰጠው ድጋፍ በአህጉሩ ውስጥ እያደገ የመጣውን የግልና የፖለቲካ ነፃነቶች ጥያቄ አሳይቷል/አንፀባርቋል። ስዋዚላንድ ነፃ የሆነ የፍትሕ ሥርዓት እንዲኖር እና ሴቶች (ከወንዶች ጋር) እኩል የሆነ ሕጋዊ ሥርዓት እንዲኖራቸው የደነገገውን ሕገ መንግስት በ32 ዓመታት ለመጀመርያ ጊዜ አውጃለች። ሆኖም፣ የአገሪቱ ዜጎች የዚህን ሕገ መንግስት በሙሉ መተግባር ገና እየጠበቁ ናቸው። አሜሪካ በአህጉሩ በሙሉ የሚገኙ የወታደራዊ ተቋም እና የሕግ አስከባሪ መሥርያ ቤቶች ስለሰብዓዊ መብቶች መርሆዎች ያላቸው ግንዛቤ እንዲሻሻል፣ የእስር ቤቶች ሁኔታ እንዲሻሻል፣ ለሴቶች እና ለአናሳዎች ስለ ሕጋዊ መብቶቻቸው ትምህርት በመስጠት፣

በሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች መካከል ትስስር እንዲኖር በማድረግ ሠርታለች። አሜሪካ በዑጋንዳ ውስጥ የሴቶችን መብት እና አቋም ለማሻሻል የተረዘጋውን ሰፊ ዕቅድ (ፕሮጀክት) ደግፋለች። ይኽም በሴቶች የፓርሊያመንት አባላት መካከል እና ከ300 በላይ የሆኑ ለአካባቢ እና ብሔራዊ መስርያ ቤት ውድድር የሚቀርቡ አንእስት እጩዎች እርስ በርስ የሚማማሩበትን ያካተተ ነበር።

በአፍሪካ የሚገኘው ልዩ ልዩ አምልኮቶች በሃይማኖቶች መካከል እና በነገዶች መካከል እንዲኖር የሚያሻውን በጋራ መቻቻል በተለየ ሁኔታ የሚያሳይ ነው። ከፍ ያለ ቁጥር ያላቸው ሙስሊም ሕዝቦች ባሉባቸው ብዙ አገሮች የራማዳንን የተቀደሰ ወር ፍፃሜ ለማክበር ከልዩ ልዩ ሃይማኖቶች ጋር አብሮ መሰብሰብ በየዓመቱ በኤምባሲ የተለመደ ሆኗል። አሜሪካ በንግግሮች እና በኢፍታር እራት ወቅት በሚደረጉ ስብሰባዎች አማካይነት በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች ከሚገኙ የሙስሊም መሪዎች ጋር የሁለትዮሽ ሃሳብ መለዋወጥን አራምዳለች። የሚፈጠሩ ሁከቶች እና በአምልኮት ነፃነት ላይ የሚጣሉ ገደቦች የሚፈጥሩትን ችግሮች በማስመልከት፣ ከፖለቲካ እና ከሃይማኖት መሪዎች ጋር በብሔራዊ እና በአካባቢ ደረጃዎች በመገናኘት፤ በአገሪቱ ስላሉት ውጥረቶች የተሻለ አስተውሎት ለማግኘ ት በሰፊው ሠርታለች።

በሰዎች መነገድን እና ብዙ የሠራተኛ መብቶች ጥሰቶችን ለማስቆም አሜሪካ በመላው አፍሪካ ከፍተኛ ሀብት አውጥታለች። እነዚህ ፕሮግራሞች በእርምጃዎቹ ተጋላጭ ለሆኑ ወጣቶች የትምህርት እና የሥራ ሥልጠና ዕድሎችን ለመስጠት፣ ከሕግ አስፈፃሚዎች ጋር ትብብር በማስፋፋት፣ እና የእርምጃዎቹ ሰለባ የሆኑትን ተመልሰው ከቤታቸው ማህበረሰቦች ጋር እንዲቀላቀሉ በመርዳት ተንቀሳቅሳለች። ለምሳሌ፣ አሜሪካ በላይቤሪያ እና በሴራ ሌዮን ድንበር ዘለል በሰዎች መነገድን ለማስወገድ መደረግ ስላለበት የግንዛቤ ፕሮግራም የሚያስፈልገውን ገንዘብ ሰጥታለች። እንደዚሁም 10,000 ያህል ለሚሆኑ አስከፊ ለሆነ የሕፃናት ሠራተኛ ነት ለተጋለጡ ወይም የመጋለጥ አደጋ ለተጋረጠባቸው ሕፃናት የትምህርት ዕድሎችን ማስፋቷን ቀጥላለች። ኬንያ፣ አንጎላ፣ የኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ፣ ዚምባብዌ፣ እና ጊኒ፣ ሌሎችን ሳይጨምር፣ የግብረ ሥጋ ረብሻን እና በሴቶች ላይ የሚፈፀም የመብት ጥሰትን በሚመለከት በእራስ ተነሳሽነቶችን በማካተት፣ ለሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ ፕሮግራም የአሜሪካን ድጋፍ አግኝተዋል።

ለሚሰራው ተጠያቂ የሆኑ መንግስታት ያላቸው፣ የፖለቲካ እና የኤኮኖሚ ነፃነት፣ እና የግለሰብ ሰብዓዊ መብቶች የሚከበሩባቸው አገሮች በልፃጋ፣ ጤናማ እና የተማሩ ሕዝቦች ለመገንባት የበለጠ ዕድል አላቸው። ግጭት፣ ትርምስ፣ ጉቦኛ እና ጨቋኝ መንግስት፣ እና የሰብዓዊነት አስጊ ሁኔታ ውስጥ መውደቅ ብዙውን ጊዜ አብረው የሚኖሩ መሆናቸው አጋጣሚ አይደለም። አሜሪካ በአፍሪካ ውስጥ ዴሞክራሲን እና ሰብዓዊ መብቶችን መደገፏን እና ማራመዷን ትቀጥላለች። ይህንንም የምታደርገው የአህጉሩ አገሮች ለሰላም፣ ለፀጥታ እና ለመረጋጋት መሰረቱን በይበልጥ እንዲያጠናክሩና እንዲያሰፉ ለመርዳት ነው።

ኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እና በገዥው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር ጥምረት የምትመራ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ናት። በግንቦት 1997 ዓ.ም. በተደረገ ፓርሊያመንታዊ ምርጫ ገዥው ፓርቲ ለሦስተኛ ጊዜ በተከታታይ ለአምስት ዓመት ወቅት አብላጫ ድምፅ ያገኘ ቢሆንም፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን መቀመጫዎች አግኝተዋል። ይኽም በኢትዮጵያ ታሪክ በፌደራል እና በክልል ፓርሊያመንቶች ውስጥ እጅግ የተለያዩ ፓርቲዎች ተሰብስበው እንዲሳተፉ አድርጓል። ሆኖም፣ ከምርጫው በኋላ የተፈጠረው ሁከት በርካታ ቁጥር ያላቸው የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ታግተው በአንዳንዶቹ ላይ የአገር ክህደት ወንጀል ክስ እንዲመሰረትባቸው አድርጓል። በ1998 ዓ.ም. ውስጥ በፌደራል ፓርሊያመንት የተቃዋሚ ፓርቲዎች ተሳትፎ ከፍ እንዲል በማድረግ እና በውይይት አማካይነት መሻሻሎችን በማራመድ፣ አገሪቱ ተጨባጭ እመርታ አድርጋለች። በዚያው ጊዜ በብዙ መስኮች ሰብዓዊ መብቶችን በሚመለከት የመንግስት ክንዋኔ ደካማ እንደሆነ ቀጥሏል። በዓመቱ ውስጥ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የሚከተሉትን የካትታሉ፦ ሕገወጥ ግድያዎች፣ ድብደባ፣ ድፍረት፤ የፀጥታ ኃይሎች ታጋቾችን እና የተቃዋሚ ደጋፊዎችን ማጎሳቆል፣ የእስር ቤት ሁኔታዎች ዝቅተኛነት፣ በተለይም ለተቃዋሚ ወገንተኛነት አላቸው ተብሎ የሚጠረጠሩትን ወይም የተቃዋሚ አባል የሆኑትን በማንአለብኝነት ማሰር እና ማገት፣ በሺሕዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ክስ ሳይመሠረትባቸው ማሰር እና የፍርድ ቤት ክስ እና ሂደት ሳይጀመር ለረጅም ጊዜ ማገት፣ የዜጎችን የግለኝነት መብት መጣስ፣ በፕሬስ ነፃነት ላይ ገደቦች ማድረግ፣ መንግስትን የሚነቅፉ መጣጥፎች በማተማቸው ጋዜጠኞችን ማሠር፣ ማገት፣ እና ማዋከብ፣ በመሰብሰብ እና ማህበር በመመስረት ነፃነት ላይ ገደቦች ማድረግ፣ በሴቶች ላይ ሁከት መፍጠር እና ሕብረተሰብዓዊ ማግለል ማድረግ፣ እና ሕፃናትን መድፈር፣ የአንእስት ግርዛት፣ ለኢኮኖሚ እና ግብረ ሥጋ ዓላማዎች ሕፃናትን መበዝበዝ፣ በሰዎች መነገድ፣ የአካል ጉዳተኞች በሆኑ ሰዎች፣ እና በሃይማኖት እና በነገድ አናሳ በሆኑት ጎብረተሰብዓዊ ማግለል መፈጸም፣ እና በማጎበራት ሥራዎች ላይ የመንግስት ጣልቃ መግባት።

የአሜሪካ ስትራቴጂ በብዙ ቁልፍ በሆኑ ግቦች ላይ አትኩሯል፦ 1) የተቃዋሚ መሪዎች ከመገለል ይልቅ እንዲሳተፉባቸው በማበረታታት ዴሞክራሲያዊ

ተቋሞችን ማጠናከር፣ 2) በመንግስት እና በተቃዋሚ ተወካዮች መካከል የሁለትዮሽ ንግግር እንዲደረግ በማነቃቃት የፖለቲካ ማሻሻል እንዲደረግ እና ዕርቅ እንዲወርድ ወደፊት መግፋት፣ 3) ከሌሎች ለጋሾች ጋር አብረን በመስራት የአገሪቱን ዴሞክራሲያዊ ተቋሞች ለማጠናከር የረጅም ጊዜ ዕርዳታ መስጠት፣ እና 4) በ1997 ዓ.ም. እና በተከታዩም ዓመት ተሰብስበው የታገቱት በሺሕዎች የሚቆጠሩ ሰዎች እንዲፈቱ ማድረግ።

የአሜሪካ መንግስት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በፌደራል ፓርሊያመንት ውስጥ በይበልጥ እንዲሳተፉ በማበረታታት እና በውይይት አማካይነት የፖለቲካ መሻሻል እንዲደረግ ወደፊት በመግፋት ንቁ ሚና ተጫውቷል። እንደዚሁም በህዳር 1998 ዓ.ም. ከተፈጠረው ነውጥ በፊት በመንግስት እና በተቃዋሚ መሪዎች መካከል የነበረው ፖለቲካዊ ውይይት እንደገና ተጀምሮ እንዲቀጥል በማበረታታት የአሜሪካ ባለስልጣኖች በሁለቱ መካከል የአስታራቂነት ጥረቶች አድርገዋል። በከፊል በአሜሪካ ባለሥልጣኖች ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶች ምክንያት፣ በዓመቱ መጨረሻ ላይ አብዛኞቹ ከተቃዋሚ ወገን የተመረጡት አባላት በፓርሊያመንት መቀመጫቸውን ይዘው ከዚያም ቀጥሎ ቁልፍ በሆኑ ዲሞክራሲያዊ ማሻሻሎች ላይ በፓርቲዎች መካከል ውይይቶች ተካሂደዋል። ከመንግስት ባለስልጣኖች ጋር ለተደረጉት ድርድሮች በተግባር የተፈተነ መሠረት ለሆነው ጥናት ማካሄጃ አሜሪካ አስፈላጊውን ገንዘብ ሰጥታለች።

አሜሪካ እና ሌሎች ለጋሽ አገሮች የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትን ለመደገፍ አንድ የተቀናጀ ፕሮግራም ጀምረዋል። አሜሪካ ለፓርሊያመንት አዲስ አባላት በሙሉ የመለማመጃ ሥልጠና እና በአመራር ላይ ለሚገኙ፣ አንእስት አባላት፣ እና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ደግሞ የተለያዩ ሥልጠና ሰጥታለች። ሥልጠናው በአካሉ የተወካይነት፣ የሕግ አውጭነት እና፣ የመቆጣጠር ተግባራት ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ እንደዚሁም በገገርው እና በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል መልካም የሥራ ግንኙነት ለማዳበር ትኩረት ሰጥቷል። አሜሪካና ሌሎች ለጋሽ አገሮች ለተወካዮች ምክር ቤት እና ለዘጠኝ ክልላዊ መስተዳድር ምክር ቤቶች የባለብዙ ወገን ድጋፍ ስለሚሰጥበት የአምስት ዓመት ፕሮግራም ለማውጣት የተለያዩ መመዘኛዎችንና ምክክሮችን አካሂደዋል። እንደዚሁም አሜሪካ፣ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድን በሚመለከት፣ በመጀመርያው ፕሮግራም አካባቢ የምርጫዎችን አመራር ለማሻሻል ስለሚወሰዱ እርምጃዎች እና፣ ከዚያም ቀጥሎ በረጅም ጊዜ እንቅስቃሴ በ2002 ለሚደረጉት ምርጫዎች የቦርዱን አቅም ወደ ዓለም አቀፋዊ

ደረጃዎች ከፍ ለማድረግ በብዙ ለጋሾች ለተደረጉት ምዘናዎች የበኩሏን አስተዋፅኦ አድርጋለች።

የብዙሀን መገናኛ(ሚዲያ) ነፃነትን፣ የመናገር ነፃነትን ወደፊት ለማራመድ የአሜሪካ መንግስት ዲፕሎማሲያዊ እና ፕሮግራማዊ ድጋፉን በሙሉ ተጠቅሟል። በዴሞክራሲያዊ ማሻሻል ላይ በፓርቲዎች መካከል ከተደረጉት ውይይቶች ጋር በማያያዝ ለፕሬስ ሕግ ረቂቅ/ከዓለምአቀፋዊ የመረጃ ነፃነት አዋጅ ጋር በሕግና ድንጋጌ ደረጃዎች ጋር በሚጣጣም ሁኔታ ከመመሪያዎች ላይ ላደረሱት ጥናቶች አሜሪካ አስፈላጊውን ገንዘብ ሰጥታለች። የአሜሪካ መንግስት በሚዲያ ባለጉዳዮች መካከል በፕሬስ ሕግ ረቂቅ፣ ብሔራዊ የፕሬስ መማክርት እንዲመሰረት በቀረበው ሃሳብ፣ እና በሚዲያ ስነምግባር ላይ ውይይት (ዳያሎግ) እንዲደረግ ሁኔታዎችን አመቻችቷል። አሜሪካ በመንግስት የዜና ማሠራጫዎች በአማራ ክልል ለሚሰሩ ባለሞያዎች በተመራማሪ ዘጋቢነት ስልጠና፣ እንደዚሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የጋዜጠኝነት ድህረ ምረቃ ትምህርት እንዲያስተምር አንድ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ምሁር ሰጥታለች። የሕዝብ ዲፕሎማሲ ገንዘብ (ፈንድስ) ጋዜጠኞች፣ ምሁራን፣ የሃይማኖች መሪዎች፣ ሌሎችም የሃሳብ መሪዎች በአለምአቀፋዊ የጎብኝዎች ልውውጥ እንዲሳተፉ አስችሏል። የአሜሪካ ድምፅ የዓፍሪካ ቀንድ አገልግሎት ሃላፊ ባለፈው ሕዳር ለጉብኝት በመጡበት ጊዜ የአሜሪካ ሹማምንት በጋዜጠኝነት ሞያ እና በንግግር ነፃነት ላይ በአካባቢ ከሚገኙ የጋዜጠኝነት ተማሪዎች ጋር ውይይት በማዘጋጀት እስተናግደዋል።

የአገሪቱ ሲቪል ሕብረተሰብ የየአካባቢው መስተዳድር ተቋሞች ለልማት ፕሮጀክትና ለአገልግሎቶች አቅርቦት የሚያደርጉት የእቅድ ዝግጅት፣ አፈፃፃም፣ ግልፅነት እና ተጠያቂነት እንዲኖረው ለማድረግ እንዲጥሩ አሜሪካ አቅማቸውን ለማጠናከር ተንቀሳቅሳለች። ለምሳሌ፣ የማህበረሰብ-መንግስት አጋርነት ፕሮግራም መቋቋም ከ 45 ,000 በላይ የሆኑ የወላጅ-መምህር ማህበረሰብ አባላት እና የትምህርት ሹማምንት፣ የትምህርት ቤቶችን ማሻሻል ጨምሮ፣ ለትምህርት ቤት አመራር ሥልጠና እንዲያገኙ አስችሏል። የአሜሪካ መንግስት ከአገሪቱ አሥራ አንድ የአስተዳደር ክልሎች በሰባቱ ውስጥ ከ10 ሚሊዮን በላይ ለሆነው ሕዝብ የተደረሰውን የዴሞክራሲ እና ሰብዓዊ መብቶች ፕሮጀክቶች ፋይናንስ አድርጓል። አሜሪካ ግቦቻቸው ስለሰብዓዊ መብቶች ማስተማርን፣ ሕዝባዊ የሁለትዮሽ ውይይት ማካሄድን፣ ግጭት ለማብረድ ቀጣይነት የሚኖረው የመንግስት-ሲቪል ሕብረተሰብ አጋርነት መገንባትን፣ ተጠያቂነትን፣ እና መልካም አስተዳደርን

ለሚያካትቱት የተለያዩ የአገር ውስጥ መያዶች ለግቦቹ ማስፈፀሚያ ገንዘብ ሰጥታለች። በሕግ መተዳደርን ለመደገፍ የአሜሪካ ሹማምንት የፖለቲካ ታጋቾች እንዲፈቱ ይፋ መግለጫዎች ከማውጣታቸውም በተጨማሪ፣ መንግስትን ለማግባበት ጥረዋል። በዚህም ጥረት ከ1997 ዓ.ም. ምርጫ በኋላ ከታገቱት ውስጥ፣ በአገር ክህደት እና በሌሎችም ከባድ ወንጀሎች ከተከሰሱት200 ያህል የሚሆኑ የተቃዋሚ ፓርቲ ከፍተኛ መሪዎች፣ የዜና ማሰራጫ፣ እና የመያድ ተወካዮች በስተቀር፣ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ተቃውሞአቸውን ያሳዩ፣ የፖለቲካ ቀስቃሾች እና የተቃዋሚ መሪዎች እንዲፈቱ ማድረግ ተችሏል። አንድ የአገር ሽማግሌዎች ስብስብ ከመንግስት ጋር ንግግር በመጀመር ዕርቅ ለማስፈን እንዲጥር እና የቀሩትን እስረኞች እንዲያስፈታ የአሜሪካ መንግስት አበረታቷል። በአገር ክህደት የተከሰሱት እና በሰፊው የሚታወቁት የተቃዋሚ መሪዎች ትክክለኛ እና የተፋጠነ ፍርድ እንዲያገኙ አሜሪካ የጠየቀች ሲሆን፣ አንድ የአሜሪካ ሹም የፍርድ ሂደቱን ለመከታተል ከሞላ ጎደል በሁሉም ተከታታይ ችሎት ተገኝቷል። እንደዚሁም አንድ ዓለምአቀፋዊ መያድ የፍርድ ሂደቱን እንዲከታተል እና እንዲገመግም ለተደረገው ውል የአሜሪካ መንግስት ወጭውን ሸፍኗል። የአሜሪካ ሹማምንት ታጋቾቹን ከመጎብኘታቸው በተጨማሪ፣ በአንድ ወቅት ከታጋቾቹ አንዱ ድንገተኛ የሕክምና እንክብካቤ እንዲያገኙ አስደርገዋል።

በዴሞክራሲያዊ መሪዎች እና በሰብዓዊ መብቶች መከበር ላይ የተመሠረቱ ሙያዊ የሕግ አስፈጻሚ አገልግሎቶችን ለማዳበር መንግሥት አቅሙን እንዲገነባ አሜሪካ ረድታለች። ሙያዊ ምርመራ ማካሄድን፣ እና ለፓሊስ ምርመራ የሚረዳ የሕክምና ማስረጃ (ፎሬንሲክ) አሰባሰብ ችሎታዎችን ለማሻሻል ለተዘረጋው የሥልጠና ኘሮግራም የአሜሪካ መንግሥት ወጭውን መሸፈኑን የቀጠለ ሲሆን፣ ለሕግ አስፈጻሚ ሠራተኞች አካዴሚክ ትምህርት እንዲሰጣቸው፣ የሕግ አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች አስተዳደራዊ እና የሥራ አመራር ችሎታዎቻቸውን እንዲያሻሽሉ፣ የፖሊስ-ማኅበረሰብ ግንኙነቶች እንዲሻሻሉ፣ እና ለአዳዲስ ወንጀሎችን እና የወንጀል ፍትሕ ጉዳዮች ምላሽ ለመስጠት አቅምን ለማጠናከር ረድቷል። ከአንድ የአገር ውስጥ መያድ ጋር በመተባበር፣ የአሜሪካ መንግሥት ከአገሪቱ በሙሉ የፍትሕ እና የደህንነት/የፀጥታ ቢሮ ሹሞችን፣ እንደዚሁም ከዘጠኝ የክልል መስተዳድሮች የፌዴራሉ መንግሥት የእሥር/የማረሚያ ቤት አስተዳዳሪዎች በአዲስ አበባ ተገናኝተው በምህረት ማድረግ ላይ እንዲወያዩ አንድ ታሪካዊ የሆነ ስብሰባ ስፓንሰር አድርጓል። በዚህም ጥረት ምክንያት በዓመቱ መጨረሻ ከ10,000 በላይ የሆኑ እስረኞች ምህረት ተደረጉላቸዋል።

አሜሪካ የአካል ጉዳተኞች በሆኑ ሰዎች ላይ የሚደረገውን ጎጠረተሰብዓዊ አድልዎ፣ በሴቶች ላይ የሚፈጸመውን መረበሽ፣ ሕፃናትን መበደል፣ በሰዎች የመነገድን ከባድ ችግሮች ለመቅረፍ ሠርታለች። ከአሜሪካ በተሰጠ ገንዘብ የተካሄደ አንድ ኘሮጀክት አንድ የአገር ውስጥ መያድ የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ያሳወቀ እና ያራመደ አንድ የሬዲዮ ኘሮግራም ለ26 ሳምንታት አሰራጭቷል። ሌላው ኘሮጀክት አጋር የሆነ አንድ የአካባቢ መያድ ሴቶች የሚጋፈጡአቸውን አድልዎ እና ጥሰት በአፋጣኝ ለማሳወቅ በአገሪቱ የመጀመሪያ የሆነው ፈጣን የመገናኛ መስመር እንዲቋቋም ረድቷል። እንደዚሁም የአሜሪካ መንግሥት በየታ ላይ የተመሠረቱ ሁከቶችን በመቅረፍ እና የሴቶችን ማኅበራዊ እና ኤኮኖሚያዊ ሁኔታ በማሻሻል ላይ ያተኮሩ ሦስት ኘሮጀክቶችን በተግባር ላይ አውሏል። አንዱ የተሳካለት ኘሮጀክት በግርዛት የተነሳ የሴቶች እና የልጃገረዶች ጤንነት ለአደጋዎች የሚጋለጥ ስለመሆኑ ሰዎች ያላቸው ግንዛቤ ከፍ እንዲል ረድቷል። የኘሮጀክቱ ውጤቶች ያመረቁ ነበሩ፡- በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ የማኅበረሰብ አባላት ልምዱ ጉጅ መሆኑን እንዲቀበሉ ማድረግ ስለተቻለ፣ ልማዳዊ አድራጐቱን በመቃወም ተናግረዋል። ስድስት የሙስሊም መሪዎች በዓርብ የፀሎት ሥርዓት ውስጥ የአንእስት ብልት መገረዝን የሚቃወም መልዕክት በቋሚነት እንደሚጨምሩ ቃል ገብተዋል።

የአሜሪካ መንግስት የሃይማኖት ነፃነትን እና መቻቻልን አራምዷል። ወደ ሙስሊም ማኅበረሰብ ዘንድ የዘለቀው የሕዝብ ዲፕሎማሲ የሃይማኖት መቻቻልን ለማራመድ በአካባቢ ዩኒቨርስቲ ቅፅር ግቢ ውስጥ ሃይማኖትን አስታክኮ እያደገ በመጣው ረብሻ ላይ ውይይት እንዲያደርጉ አንድ ጉባዔ መጥራትን፣ በሃይማኖት እና በነገድ ላይ ስለተመሰረቱ የተማሪዎች ረብሻ መንስዔዎች ከተማሪ መሪዎች እና ከመምህራን (ፋከልቲ) ጋር አብሮ መሥራትን ያካተተ ነው።

በአገሪቱ ውስጥ በሰው የመነገድ ሰለባ በሆኑት ቁጥራቸው ከፍ ያለ ሰዎች ላይ ላተኮረው አንድ ፕሮግራም ማካሄጃ አሜሪካ ገንዘብ መስጠቷን ቀጥላለች። ፕሮግራሙ በጠቅላላው በሕዝብ እና በመንግሥት ባለስልጣኖች ዘንድ በሰው መነገድን የሚቃወም ዘመቻ ማካሄድን ያካተተ ሲሆን፣ እንደዚሁም አድራጎቱን ለመከላከል፣ የተግባሩን ፈፃሚዎች ለፍርድ ለማቅረብ፣ ሰለባ ለሆኑትም ጥበቃ ለማድረግ የሚረዱ ክፍሎችንም ጨምሯል። የሠራተኛ ፍልሰትን የሚመለከት ፖሊሲ እንዲቀረፅና በሰው መነገድን ለመከላከል በሰው መነገድን የሚያወግዝ፣

ለሰለባዎቹ ጥበቃ የሚያደርግ፣ በሰው የሚነግዱ ለፍርድ እንዲቀርቡ የሚደነግግ ሕግ እንዲወጣ ፕሮግራሙ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት ባለስልጣኖችን፣ የአካባቢ መያዶችን፣ የሲቪል ማኅበረሰብን ተቋማዊ አቅም አጠናክሮአል። በሰው የመነገድ ሰለባ የሆኑትን ለመደገፍ እና ከየማህበረሰባቸው ጋር መልሶ ለማዋሃድ፣ መጠለያ፣ የሕክምና እንክብካቤ፣ ምክር፣ ልብስ፣ እና የንጽሕና ጥበቃ በአዲስ አበባ ውስጥ ተሰጥቷቸዋል።